## ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ ለታህሳስ 5 ቀን 2007 ዓ.ም በአዲስ አበባ ለተጠራው ሕዝባዊ ሰላማዊ ሰልፍ የተላለፈ መልዕክት፡፡

### *የተከበራችሁ ጥሪያችንን አክብራችሁ በሰላማዊ ሰልፉ የተገኛችሁ የአ/አ እና አካባቢው ነዋሪዎች እና መላው የኢትዮጵያ ሕዝቦች!*

እንደሚታወቀው ሁሉ በመጪው ግንቦት ድፍን ሃያ አራት አመታት የሚያስቆጥረው ሕወሃት መራሹ ኢሕአዴግ የደርግን አምባገነናዊ መንግስት አስወግዶ ስልጣን ሲይዝ፣ የተሻለ ዘመን መጥቶ ሀገራችን ሁሉም ዜጎቿ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ሰፍኖ በእኩልነት የሚኖሩባት ትሆናለች በሚል ተስፋ፣ ስርዓቱን በጥሩ ስራዎቹ እየደገፉ በመጥፎ ተግባሩ እየወቀሱ በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ ለዚህች ሀገር ይበጃል የሚል ግምት የተወሰደበት ወቅት ነበር፡፡

ይሁን እንጂ ኢሕአዴግ ብዙም ሳይቆይ ድብቅ ፀረ-ዴሞክራሲ የአምባገነንነት ዓላውን «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» በሚል ጉራማይሌያዊ አስተሳሰብ ተግባር ላይ ማዋል ጀመረ፡፡ በዚህ ተግባሩም፣ ለሀገር ጥቅምና ለሕዝቦቿ እድገት በማሰብ፣ ያሉትን ችግሮች ተቋቁመው ለመስራት በመወሰን፣ የሽግግር መንግስቱ ተወካዮች ምክር ቤት የገቡትን ሕዝባዊ ሀይሎች፣ በጦር መሣሪያ ሀይል ጭምር ተጠቅሞ በማባረር፣ ምክር ቤቱን የግሉ መገልገያና የጥቂት አጎብዳጆቹና ወዳጆቹ መጠቀሚያ በማድረግ፣ የሽግግሩን ወቅት አጀንዳ ማክሸፉን በከፍተኛ ቁጭት የምናስታውሰው ነው፡፡ ከዚያም የሀገሪቱ ዜጎች የምንተዳደርበትንና የሀገሪቱ ሕጎች ሁሉ የበላይ ሕግ የሆነውን ሕገ-መንግስት፣ የጉዳዩ ባለቤት የሆነውን ሕዝብ ነፃና ፍትሃዊ በሆነ አግባብ ሳያሳትፍ፣ በማወጁ ምክንያት እነሆ በሕዝባችን መሃከል ጥርጣሬና ያለመተማመን እንዲሰፍን ምክንያት ፈጥሯል፡፡ በዚህም ለዴሞክራሲ፣ ለሕግ የበላይነትና ለሀገራችን ዜጎች እኩልነትና ሰብዓዊ መ ብት መከበር የሚደረገ ውን ትግል በታትኖ ላቋቋመው መንግስት «ልማታዊ» የሚል የቅፅል ስም ሰጥቶት የአንድ ፓርቲ አምባገነናዊ አገዛዝ አስፍኖ ይገኛል፡፡ ልማት በማስፋፋት ስም ደግሞ በግብታዊና ህገ-ወጥ አሠራር ሕዝብን በስፋት በማፈናቀልና መሬትን በመውረር ሕዝብን ለችግር የማጋለጥ እርምጃዎች እየተወሰዱ መሆናቸው በእጅጉ አሳዛኝ እንደሆነ መድረክ ይገነዘባል፡፡ ይህና ለሎችም የህግ የበላይነት ያልተከበረባቸው አሠራሮች ህዝባችንን በእጅጉ እየጎዳው ይገኛል፡፡ በአጠቃላዩም የኢሕአዴግ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ፖሊሲዎች ሰፊውን ህዝባችንን ለከባድ የኑሮ ውድነትና የተጎሳቆለ ህይወት ዳርጎት መገኘቱ የኢሕአዴግን ብዙሃንን አግላናይና በመስና የተጨማለቀ የልማት ፖሊሲ ክስረት የሚያጋልጥ መሆኑ ሊጤን የሚገባው አሳሳቢ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከወገንተኝነትና አድሎአዊ አሠራሮች የሚመነጨው ኢ-ፍትሃዊ የግብር ጫና ሠርቶ በሚኖረው ህዝባችን ላይ

ማረፍ፣ ሀገሪቱን ለከፍተኛ ክስረት እየዳረገ መሆኑ መድረክ ያጤነው አሳሳቢ ጉዳይ ነው፡፡ እንደዚሁም ኢሕአዴግያዊ የልማት ፖሊሲ ውጤቶች እንደሆኑ በካድሬዎቹ በስፋት የሚነገርላቸው አገልግሎቶች ማለትም - የውሃ፣ የመብራት፣ የትራንፖርት፣ ስልክና ሌሎች - ብቃት ያለው አገልግሎት መስጠት ያለመቻላቸው ሰፊውን ህዝብ ለከፍተኛ ችግር ማጋለጡ በእጅጉ የሚያሳስብ በመሆኑ መድረክ ዘወትር ሲያወግዘው የኖረ እውነታ ነው፡፡

እነዚህና ሌሎችም የተሳሳተ ኢሕአዴግያዊ ፖሊሲዎች ውጤት የሆኑ የኑሮ ቀውሶችም ሆኑ የሀገር ግንባታ ጥያቄ ዎች ምላሽ የሚያገኙት ሀገራችን ዴሞክራሲያዊ ስርዓተ-መንግስት ሲኖራት መሆኑን በመገንዘብ፣ መድረክና አባል ድርጅቶቹ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ መድረኮችን እየፈጠርን፣ ከእንግዲህ ኢትዮጵያ ሀገራችን በጠመንጃ ስልጣን ወደ መቀማማት መመለስ የለባትም ብለን በሠላማዊ መንገድ ትግላችንን ለመቀጠል መወሰናችንን ማስገንዘብ እንወዳለን፡፡ ስለሆነም በእልህ አስጨራሽ ጉዞዎች ውስጥም እየሆንን በምርጫዎች እየተወዳደርን በማሸነፍ በክልልና በፌዴራል ምክር ቤቶች የተወሰኑ አባላትን በማስገባት የሕዝቦቻችንን መብትና የሀገራችንን ሉዓላዊነት ለማስከበር ስንታገል ቆይተናል፡፡ በነዚህም መድረኮች በመጠቀም ዘወትር በሕዝቦቻችን ላይ እየደረሱ ያሉትን መከራና ብሶቶችም አስተጋብተናል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥም ለሀገራችን ፖለቲካዊ ችግሮች መፍትሔ መፈለግ ያለበት ብቸኛው መንገድ በነፃና ፍትሃዊ ዴሞክራሲያዊ ምርጫዎች፣ ፓርቲዎች ተወዳድረው እና በውሳኔ ሕዝብ /ሪፈረንደም ወዘተ/ ለችግሮቹ የመፍትሔ አማራጮች በሚያስቀምጧቸው መሠረት፣በሠለጠነ መንገድ መፍትሔ መሻት ብቸኛው መንገድ መሆኑን እየገለጥን ታግለናል፡፡

ይህንን የፖለቲካ ችግሮች መፍቻ ሰላማዊ ስልት ተግባራዊ ለማድረግ ከ1997 ዓ.ም ምርጫ በፊት፣ በለጋሽ መንግስታት እና በሌሎች ባለድርሻ አካላት አመቻችነት፣ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ማካሄድ ስለሚቻልበት ሁኔታ ከገዢው ፓርቲ ጋር በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት አማካይነት ያደረግነው ድርድር፣አንፃራዊ መሻሻል ለታየበት የ1997ቱ ምርጫ እንዳበቃን የሚታወስ ነው፡፡ በዚሁም ኢሕአዴግ የፖለቲካ ምሕዳሩን ትንሽ በመክፈቱ፣ ሕዝባች ን ሁኔታውን ተጠቅሞ በ1997ቱ ምርጫ የታየውን ውጤት ሊያስመዘግብ ችሎአል፡፡ ከዚያም በመቀጠል አዲስ የምርጫ ሕግ ለማዘጋጀት በተደረገው ጥረት ውስጥ ከፍተኛ ትግል ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ በጎ ጅምር በኢሕአዴግ ግትር አቋምና የድርድሩን ስነ-ምግባር በመጣስ ምክንያት መቋረጡ በሰላማዊ አግባብ ለፖለቲካው ችግሮቻችን መፍትሄ እንዳይፈለግ ተስፋ አስቆራጭ ሆኖ ቀጥሏል፡፡

በ1997ቱ የምርጫ ምሕዳር ድርድሩ አማካይነት በተሻሻለው የምርጫ ውድድር አጋጣሚ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ተጠቅመው ያስመዘገቡት የምርጫ ውጤት ክፉኛ ያሳሰበውና ያስደነገጠው ገዢው ፓርቲ፣ ከ1997 የምርጫ ሂደት በፊት የተደረሰባቸውን ስምምነቶች ሁሉ በመቀልበስ በወሰዳቸው ፀረ-ዴሞክራሲያዊ እርምጃዎች ምክንያት፣ በ2002 ምርጫ ከአጋር ፓርቲዎቹ ጋር በመሆን ብቸኛ አሸናፊነቱን አውጇል። በመሆኑም ገዢው ፓርቲ የሃገሪቱ መንግስታዊ ስልጣን የበላይ የሆነውን ፓርላማ በብቸኝነት ይዞ በህዝቡ ላይ ያልተገደበ መንግስታዊ ስልጣኑን በመጠቀም የተለያዩ ጫናዎችን እያሳረፈ፣ ተቃዋሚ በሌለበት በአፈናና በጉልበት ሃገሪቱን በአምባገነንነት እየገዛ ይገኛል። ይህ በእጅጉ ኋላ-ቀር አምባገነናዊ ስርዓተ-መንግስት ብዙሃኑን ሕዝባችንን በስልጡኑ በፓርቲዎች ሰላማዊ የምርጫ ውድድር አማካይነት፣ የስልጣኑ ባለቤት የመሆኑን ሕገመንግስታዊ መብት ገድቦ ይገኛል። መላውን ሕዝባችንንም ከጊዜ ወደ ጊዜ በምርጫዎች ፋይዳ ላይ ተስፋ እንዲቆርጥ እያደረገው ይገኛል። በመሆኑም ይህ ኢሕአዴግ የመረጠው “በአንድ አውራ ፓርቲ” ብቸኛ ቁጥጥር አገርን የመግዛቱ የአምባገነን ስርዓተ-መንግስት መገለጫ ለሃገራችን አደገኛ የመሆኑ ሁኔታ በእጅጉ እያሳሰበን፣ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት የመገንባቱ ተስፋችን ጨርሶ እንዳይከስም፣ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫዎች የሚካሄዱበትን ሁኔታ ለመፍጠር ገዢው ፓርቲ ከሃቀኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር እንዲደራደር በተደጋጋሚ ስንጠይቅ ቆይተናል።

በአንፃሩም የኢትዮጵያ የሠላማዊ ትግል መርህ አራማጆች ተስፋ ሳንቆርጥ እየተቀራረብን ለአንድ አመት ያህል በመነጋገርና ካለፉት ተሞክሮዎች በመማር እልህ አስጨራሽ ድርድር ካካሄድን በኋላ፣ አዲስ የጋራ ማታገያችን የሆነውን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ /መድረክ/ በመፍጠር ለነፃና ፍትሃዊ ምርጫ እውን መሆን የምናካህደውን ትግል ተያይዘነዋል። እኛ ምን ጊዜም ለሠላማዊ ትግልና ለጠረጴዛ ዙሪያ ድርድርና ውይይት ኢሕአዴግን ከመጋበዝ የታቀብንበት ወቅት የለም። ኢሕአዴግ ግን ጆሮ ዳባ ልበስ በማለት በአፍራሽ አድራጎቱ ቀጥሎአል።

## ክቡራትና ክቡራን የሰላማዊ ሰልፉ ተሳታፊዎች፣

በመሠረቱ ምርጫ የዴሞክራሲያዊ መንግስት ስልጣን ሽግግር መሣሪያ፣ የአንድ ሀገር ሕዝብ ሉአላዊነትና የስልጣን ምንጭነት ማረጋገጫና የዜጐች ዴሞክራሲያዊ መብቶች መገለጫ መሆኑን በማመን፣ ባለፉት ምርጫዎች መድረክና አባል ድርጅቶቹ ሲሳተፉና ተሳትፎ ለማድረግም ከፍተኛ ጥረቶች ሲያደርጉ ቆይቷል። በዚህ የሠላማዊ ትግል ጉዞአችን ኢሕአዴግ ከመጠን ያለፉ ጥቃቶችን ቢያደርስብንም፣ እጅግ አስቸጋሪና አደገኛ ሁኔታዎች ውስጥ መራጭ ህዝባችንን በማስገባት ያስከፈልነው መስዋእትነት ዘግናኝ ነው። ይህም እስከ ሕይወት

መስዋዕትነት ድረስ የተከፈለበትና አለም አቀፍ እና ሀገራዊ ነፃ ዘጋቢዎች የመዘገቡት፣ የኢሕአዴግ መንግስትም በተወሰነ ደረጃ የተቀበለው ሃቅ ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ለሀገሪቱ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ የበኩላችንን አስተዋጽዖ ለማድረግ ለምናደርጋቸው ተሳትፎዎች፣ በገዢው ፓርቲ ኢሕአዴግ የሚፈጠሩ ኢ-ዴሞክራሲያዊ ሁኔታዎች ተቀርፈው፣ የኢትዮጵያ ምርጫ አፈፃፀም ችግሮች እንዲወገዱ የመድረክ አባል ድርጅቶች በተናጠልና ከሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር በመጣመር፣ደጋግመን ጠይቀናል። ከነዚህም ውስጥ በጥቅምት ወር 2005 ዓ.ም በአዳማ ከተማ በ2005ቱ የአካባቢ ምርጫ የጊዜ ሠሌዳ ላይ ለመመካከር የምርጫ ቦርድ በጠራው ስብሰባ ላይ ከምርጫ አፈፃፀም የጊዜ ሠልዳ እወጃ በፊት በ2002 ምርጫ ወቅት የታየው የገዢው ፓርቲ የአፈና እና የሸፍጥ አካሄድ እስካልተወገደ ድረስ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ማካሄድ እንደማይቻል ገልፀን፣ በምርጫ ችግሮች እና መፍትሄዎቻቸው ዙሪያ ኢህአዴግ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር የሚወያይበትና የሚደራደርበት ስብሰባ በቦርዱ እንዲዘጋጅ በህብረት የጠየቅነው የሚታወስ ነው። ቦርዱም ስብሰባውን ለማዘጋጀት ቃል ከገባ በኋላ ቃሉን አጥፎ ለነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ተገቢው ነባራዊ ሁኔታ መኖሩ ሳይረጋገጥ የምርጫ ጊዜ ሠሌዳውን በማወጁ፣ በህገመንግስቱና በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣንና ሃላፊነት የምርጫ ቦርድ የመወጣት ፍላጐትና ቁርጠኝነት እንደሌለው መድረክ በመረዳት፣ ነፃ ውድድር ከሌለበት የ2005ቱ የአካባቢያዊ ምርጫ ሳይወድ በግድ ተገፍቶ መውጣቱን በቁጭት የምናስታውሰው ነው።

ክቡራትና ክቡራን የሰላማዊ ሰልፉ ተሳታፊዎች፣

ወቅቱን የጠበቀ ምርጫን ማካሄድ ከዴሞክራሲያዊ ስርዓት መገለጫዎች መሃከል አንዱ እንደመሆኑ፣ ኢሕአዴግም ስርዓተ-መንግስቱን ዴሞክራሲያዊነት፣ለጋሽና አበዳሪ የዓለም መንግስታትና ድርጅቶች እንዲያዩለት ከመፈለግ ዓላማው በመነሳት አስመሳይ ምርጫዎችን በየወቅቱ ያውጃል። በዚህ ሁሌ በእንከን የተሞላና ዓለም አቀፍ ደረጃን ባልጠበቀና ተአማኒነት የጎደለው ኢ-ዴሞክራሲያዊ ተግባር ላይም፣ የሀገራችንን ሀብት እያዋለ፣ «ተመረጥኩ» በማለት፣ በቁጥጥሩ ስር ባለው የሕዝባችን ንብረት በሆነው መገናኛ ብዙኃን የሀሰት ፕሮፓጋንዳ ዘወትር ያስተላልፋል። ነፃ ፍትሃዊና ተዓማኒ ምርጫን በሚመለከት ላለብን ችግርች ዋነኛው በኢሕአዴግና በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መካከል ያለው መመሳጠር ስለመሁኑና በዚህ ሕገ-ወጥ ተግባሩ ምርጫ ቦርድ የኢህአዴግ ብቸኛ ጉዳይ ፈፃሚነቱን በማረጋገጥ፣ በገለልተኛነቱ ላይ እየተነሳ ላለው ጥያቄ ማረጋገጫ ስመስጠቱ ጥቀት ማሳያዎችን እንጠቀሳለን፣

- ኢሕአዴግ ታማኝ ፓርቲዎችን «በተቃዋሚነት» ስም በማሰባሰብ "የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ተፈጥሯል" በማለት በምርጫ ውድድር አሯሯጭነት ማሰለፉን፣ ከዚያም በምርጫው ሙሉ ለሙሉ አሸነፍኩ ማለቱና፣ ቦርዱም ለኢህአዴግ የአሸናፊነት

ቡራኬ መስጠቱና ይህም ሁኔታ መላው መራጭ ህዝባችን በትዝብትና በቁጭት ያየው ክስተት መሆኑ፣

- ከዚህም ቀጥሎ ኢህአዴግ የነዚህን ታማኝ ፓርቲዎች ውለታ ለመመለስ፣ ለፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግስት የሚሰጠው ድጋፍ የሚከፋፈልበትን አሰራር ለመደንገግ ከወጣው ደንብ ውጪ የገንዘብ ድጋፍ ሲያከፋፍል መቆየቱ፣
- ከ1997 ዓ.ም ምርጫ በኋላ ኢህአዴግ የፖለቲካ ምህዳሩን ከመቼውም ጊዜ በላይ በመዝጋት ተቃዋሚ ፓርቲዎች መፈናፈኛ እንዲያጡ አድርጐ እንቅስቃሴያቸው በተገታበት በአሁኑ ወቅት፣ በምርጫ ህግ አዋጅ 532/2000፣ አንቀጽ 58 ላይ ከተቀመጠው የምርጫ ቅስቀሳ የጊዜ ሠሌዳ በፊት፣ ኢህአዴግ ከወዲሁ በብዙ መቶ ሚሊዮን የሚገመት የመንግስት ሃብት እያባከነ በህገ ወጥነት፣ ከሠፈር ባልቴቶችና አዛውንት አንስቶ እስከ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና ፕሮፌሰሮች ድረስ፣አዋጅ 573/2000 አንቀጽ 57 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገውን በመጣስ፣ ለረዥም ቀናት በተፅእኖ እየሰበሰበ፣ የራሱን የፓርቲ ፖሊሲ በህብረተሰቡ ውስጥ ለማስረጽ የኢንዶክትሪኔሽን ዘመቻ በሰፊው እያካሄደ፣ የምርጫ ውድድር ስነምግባር ሲጥስ፣ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ በአዋጅ ቁጥር 662/2002 መሠረት እርምጃ መውሰድ ሲገባው ዝምታ መምረጡ፡፡

ስለሆነም ቦርዱ ከኢህአዴግ ሙሉ ለሙሉ ተፅእኖ ነፃ መሆኑ ሳይረጋገጥ እና ሌሎችም መጠነ-ሰፊ የምርጫ አፈፃፀም ችግሮች ሳይወገዱ፣ እንደተለመደው ህዝባችን አማራጭ በሌለው ምርጫ በተለያዩ የኢህአዴግ ማስፈራሪያዎችና ተፅእኖዎች ጫና በግዳጅ እየተመዘገበ ኢህአዴግን እንዲመርጥ፣ የ2007 ምርጫ የጊዜ ሠሌዳ በአሁኑ ወቅት መታወጁ እንዲያው የግብር ውጣ ስራ እንጂ ፋይዳ ያለው እርምጃ አይደለም፡፡

ስለዚህ ቦርዱ በተሻሻለው የኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 7 ንዑስ ቁጥር 2 መሠረት ምርጫውን ነፃና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ለማካሄድ የሚቻልበትን ሁኔታ ለማመቻቸትና ለማረጋገጥ የተሰጠውን ስልጣን በመጠቀም፣ ከምርጫው በፊት በኢትዮጵያ የምርጫ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው ዙሪያ በመወያየት የጋራ መፍትሄ የሚፈለግበት፣ ሃቀኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከገዢው ፓርቲ ኢሕአደግ ጋር የሚደራደሩበትን መድረክ በማዘጋጀት፣ ሕገ-መንግስታዊ ኃላፊነቱን እንዲወጣ በአጽንኦት እንጠይቃለን፡፡ ይህንን ሳያደርግ ቢቀር፣ በህዝብ የነፃ ድምጽ ውሳኔ እያገኘ መጐልበት ባለበት ሰላማዊ ዴሞክራሲያዊ ሂደት ላይ፣ በኢህአዴግ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚፈፀመው ደባ ህዝባችን ተስፋ እየቆረጠ መሆኑን ማስገንዘብ እንወዳለን፡፡ ይህም በምርጫ ላይ እምነት የማሳጣት ሁኔታ ሀገራችንን ወደ አላስፈላጊ አቅጣጫ ለመምራት ለሚሹ የቀኝ አክራሪ ሃይሎች መጠናከሪያ ምክንያት እንዳይሆን ያለንን ስጋት በአንክሮ እንገልፃለን፡፡

**ክቡራትና ክቡራን የሰላማዊ ሰልፉ ተሳታፊዎች፣**

የዛሬው ሰላማዊ ሰልፍ እንዲጠራ ያስፈለገውም ይህን ሀገራዊና አንገብጋቢ ጉዳይ ለህዝባችን ገልጠን ህዝባችን በዚህ ረገድ በቀጣይ ለምናደርጋቸው ተከታታይ ትግሎች ከጎናችን ቁሞ ይኽንን የተዘጋውን የፖለቲካ ምንዳር በማስከፈት ምርጫው ተአማኒ፣ ፍትሐዊ፣ዴሞክራሲያዊና ነፃ ሆኖ እንዲካሔድ ኢሕአዴግ ብቃት ካላቸውና በምርጫ የመወዳደር እቅድ ካላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር እንዲደራደር ለመጠየቅ እና ሌሎችንም እጅግ አሳሳቢ የሆኑ ሕዝባዊ ጉዳዮችን ጭርም ለማንሳት ነው፡፡ ስለሆነም፣

**1ኛ. ገዢው ፓርቲ ኢሕአዴግ እና መንግስቱ - ወደ ምርጫው አፈፃጸም ከመጣደፍ በፊት በምርጫው ላይ መራጭ ህዝብ እምነት እንዲያድርበት ለሚከተሉት ጥያቄዎቻችን ተገቢውን አስቸኳይ ምላሽ እንዲሰጥ አበክረን እንጠይቃለን፣**

1.1 ኢሕአዴግ ቀደም ሲል መድረክና «ሰላሳ ሶስቱ የአዳማ ፒቲሽን ፈራሚዎች» ላቀረቡት ጥያቄዎች መልስ እንዲሠጥ፣

1.2 መድረከ እንነጋገርባቸው ብሎ ስለ ምርጫና ተዛማጅ ጉዳዮች ባቀረባቸው ነጥቦች ላይ ኢሕአዴግ ባስቸኳይ ድርድር እንዲጀምር፣

1.3 ለዲሞክራሲያዊ ጥያቀዎችን በማንሳት ሲታገሉ ኢ-ሕገመንግስታዊ በሆነ መንገድ የታሠሩ ፖለቲከኞችና የሙስሊሙ ማህበረሰብ ችግሮች መፍትሄ አፈላላጊዎች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ፣

1.4 ለምርጫ መካሔድ እጅግ አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች አንዱና አራተኛው የመንግስት ክንፍ የሚባለው ነፃ ፕሬስና ሚዲያ ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ አለ ተብሎ የሚነገር ጉዳይ አይደለም፡፡ ስለሆነም የመያ ግዲተቸውን ሲወጠ ያለአግባብ ተወንጀው ወደ ወህኒ የተወረወሩ ጋዜጠኞችና ጦማርያን በአስቸኳይ እንዲፈቱ፣

1.5 ሕዝባችን በአንድ ለ5 መረብ አፈናና ቁጥጥር ከሚካሄድ የምርጫ ድምጽ አሰጣጥ ነፃ እንዲሆን መዋቅሩ ባስቸኳይ እንዲፈርስ፣

1.6 በኢሕአዴግ ካድሬዎች ሲከናወማን የኖረው የምርጫ አስፈፃሚነት አሰራር በገለልተኛ ባለ ሞያ ተቀጣሪዎች እንዲከናወን ማድረግ፣

1.7 ህዝብ በሰላማዊ አግባብ በነፃነት መደራጀት እና አላማውንም ለማስፈፀም የመንቀሳቀስ መብትና፣ በህጉ መሠረት የተደራጁ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫዎች መሳተፍንና አላማቸውንም ለማስፋፋት በህዝቡ መሃከል መንቀሳቀስን የሚመለከቱ ጉዳዮች በሀገሪቱ ህገ-መንግስት ድንጋጌ መሠረት፣ ለፌዴራል መንግስት ሃላፊነት የተሰጠ መሆኑ እየታወቀ፣ በትግራይ ክልል የመቀለ ማዘጋጃ ቤት ህገ-መንግስትን የጣሰ ህግ ወጥቶ

የመድረክ አባል የሆነው ዓረና ትግራይ መንቀሳቀስ የማይችልበት ሁኔታ በመፈጡሩ ይኸው ህገ-ወጥ ገደብ ባስቸኳይ እንዲነሳ፣

1.8 በሰላማዊ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች አባላት ላይ እየተካሄደ ያለው እስራትና ወከባ ባስቸኳይ እንዲቆም፣

1.9 በምርጫ ወቅት በምርጫ ጉዳዮች ፈጣን ውሳኔ የሚሰጡ ነፃና ገለልተኛ ፍርድ ቤቶችን በየምርጫ እርከኑ ማቋቋም፣

1.10 ነፃ የሀገር ውስጥና የውጭ ሃገር ታዛቢዎች ምርጫውን በነፃነት የሚከታተሉበትና የሚታዘቡበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

2ኛ. መላው የሀገራችን ሕዝቦች - ይኸንን የኢሕአዴግ የማንአለብኝነት የምርጫ አፈፃፀም አደገኛ አካሔድ አጢነው፣ ኢሕአዴግ ከዚህ አካሔዱ ታቅቦ ለሀገር የሚበጅ የምርጫ ምህዳር ድርድር ጥያቄን ተቀብሎ ድርድሩ እንዲካሔድ ተገቢውን ተፅዕኖ እንዲያደርጉ ጥሪ እናስተላልፋለን።

3ኛ. ሃቀኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች - የጋራ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች በአጠቃላይና በምርጫው ጉዳይ ላይ በተለይ በጋራ በመሆን ጥያቄዎቻችንን እንድናቀርብ መድረክ የትብብር ጥሪውን እያቀረበ፣ ለዚህ ትግላችን በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጪ የምትገኙ መላው የሀገራችን ዜጎች በማናቸውም መልኩ እገዛችሁና ድጋፋችሁ እንዳይለየን ሀገራዊና ታሪካዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

4ኛ. የኢትዮጵያ ወዳጆች ለሆኑ የዓለም መንግስታትና ድርጅቶች - ወዳጅነታችሁ በአጠቃላይ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር እንጂ ከኢሕአዴግ ጋር ብቻ አለመሆኑን ተገንዝባችሁ፣ ለዘንድሮው የሀገራችን ምርጫ መሳካት በኢሕአዴግ ላይ የበኩላቸውን ተፅዕኖ እንድታሳሩ እና የበኩላችሁን ድጋፍ ለነፃ ፍትሃዊና ተዓማኒ ምርጫ እንድታደርጉ ጥሪያችንን እናስተለልፋለን።

ቸሩ ፈጣሪያችን ኢትዮጵያንና ሕዝቦችዋን ይጠብቅ!!

አመሠግናለሁ!

ታህሳስ 5 ቀን 2007 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>